# የመመስረቻ ጽሁፍ ማሻሻያ የውሳኔ ሃሳቦች

## ኅዳር 2018 ዓ.ም

### 1. አግባብ ባላቸው ሕጎች መሰረት ማሻሻያ የተደረገባቸው

| ተ.ቁ | ነባሩ የመመስረቻ ጽሁፍ አንቀፅ/ቁጥር | አሁን ላይ ያለው የመመስረቻ ፅሁፍ | የማሻሻያ ሃሳቦች |
|---|---|---|---|
| 1 | 4 (4.19) | ከዚህ በላይ በግልጽ ከተዘረዘሩት ውጪ በሌሎች የተለመዱ የንግድ ባንክ ስራ በሆኑ ተግባራት ላይ መሰማራት | - ከዚህ በላይ በግልጽ ከተዘረዘሩት ውጪ በሌሎች የተለመዱ የንግድ ባንክ ሥራ በሆኑ እና አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ባንኮች እንዲሰማሩባቸው በሚፈቀዱ ተግባራት ላይ መሰማራት |
| 2 | 5(5.1 እና 5.2) | - የባንኩ ካፒታል ብር 20,000,000,000.00 (ሃያ ቢሊዮን ብር) ሲሆን፣ የእያንዳንዱ ዋጋ ብር 1,000 (ብር አንድ ሺህ) በሆኑ 20,000,000.00 (ሃያ ሚሊዮን) የተመዘገቡ ተራ አክስዮኖች የተከፋፈለ ነው። ከዚህም ውስጥ ብር 5, 000, 000, 000 (ብር አምስት ቢሊዮን) ተከፍሏል።<br>-የባንኩ የተፈረመ ካፒታል ብር 5 ቢሊዮን ነው። | - የባንኩ ካፒታል ብር 20,000,000,000.00 (ሃያ ቢሊዮን ብር) ሲሆን፣ የእያንዳንዱ ዋጋ ብር 1,000 (ብር አንድ ሺህ) በሆኑ 20,000,000.00 (ሃያ ሚሊዮን) የተመዘገቡ ተራ አክስዮኖች የተከፋፈለ ነው። ከዚህም ውስጥ ብር 8,120,629,560.00 (ብር ስምንት ቢሊዮን አንድ መቶ ሃያ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ስድሳ) ተከፍሏል።<br>- የባንኩ የተፈረመ ካፒታል ብር 11,665,497,000.00 (ብር አስራ አንድ ቢሊዮን ስድስት መቶ ስድሳ አምስት ሚሊዮን አራት መቶ ዘጠና ሰባት ሺህ) ነው። |
| 3 | 6(6.2) | ለተከፈለባቸው አክስዮኖች የባለአክስዮኑን ስም የያዘ የአክስዮን ሰርተፊኬት ለባለአክስዮኑ ይሰጣል፤የሰርተፊኬቱ ይዘትም በሕግ በተቀመጠው መሰረት ይሆናል። | • የተከፈለባቸው አክስዮኖች በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን አስቀድመው ከተመዘገቡ በኋላ ወደ ባለአክስዮኑ ማዕከላዊ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግምጃ ቤት የአክስዮን ሂሳብ ገቢ ይደረግለታል።የአክስዮን ባለቤትነትም በማዕከላዊ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግምጃ ቤት በኤሌክትሮኒክስ ምዝገባ ስርዓት የሚረጋገጥ ይሆናል። |
| 4 | 6(6.3) | ማንኛውም ባለአክስዮን ከባለቤቱ/ከባለቤቷ/ እና ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች ከሆነ የመጀመሪያ ደረጃ የስጋ ዝምድና ከሚቆጠር ጋር በነጠላም ሆነ በጋራ በመሆን ከባንኩ ጠቅላላ የተፈረሙ አክስዮኖች ከአምስት በመቶ(5%) በላይ መያዝ አይችልም ። | • ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ከባንኩ የተፈረመ ጠቅላላ አክስዮኖች ውስጥ ከሰባት በመቶ (7%) በላይ ቀጥተኛ የአክስዮን ድርሻ ሊይዝ አይችልም። |
| 5 | 6(6.4) | የህግ ሰውነት ያለው ማንኛውም ተቋም ከባንኩ የተፈረሙ አክስዮኖች ከአምስት በመቶ (5%) በላይ አክስዮን መያዝ አይችልም። | • ማንኛውም በሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል ከባንኩ የተፈረሙ አክስዮኖች ውስጥ ከአስር በመቶ (10%) በላይ ቀጥተኛ የአክስዮን ድርሻ መያዝ አይችልም። |
| 6 | 11(11.1)<br>(11.2) ሆኖ የሚቀየር | የባለአክስዮኖችን ስም ዝርዝር ካላቸው አክስዮን ይዞታ ጋር የያዘ መዝገብ ባንኩ በዋና ፅ/ቤቱ መያዝ አለበት። አያያዙም በወረቀትና አስተማማኝ በሆነ የኤሌክትሮኒክስ ዘዴ መሆን አለበት። | • የባለአክስዮኖችን ስም ዝርዝር ፤ አድራሻ፤ፆታ፤የተፈረሙና የተከፈሉ አክስዮኖቻቸውን ብዛትና የገንዘብ መጠን እንዲሁም ድምጽ የመስጠት መብታቸውን የሚያሳይ ከማዕከላዊ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግምጃቤት መዝገብ ጋር ሊናበብ የሚችል መዝገብ ባንኩ በዋና ፅ/ቤቱ መያዝ አለበት። |
| 7 | 11(11.2)<br>(11.3) ሆኖ የሚቀየር | መዝገቡ የባለአክስዮኖችን ስምና አድራሻ፤ ዜግነት፤ የአክስዮን ብዛት፤ የአክስዮን መለያ ቁጥር፤ የተከፈለውን የካፒታል መዋጮንና የተመዘገቡበትን ቀን ማካተት አለበት። | • መዝገቡ የባለአክስዮኖችን ስምና አድራሻ፤ ዜግነት ፤ የአክስዮን ብዛት፤ የካፒታል መጠን፣ የአክስዮን መለያ ቁጥር፤ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ብሔራዊ የመታወቂያ ቁጥር፣ የኢሜል አድራሻ እና የተመዘገቡበትን ቀን ማካተት አለበት። |
| 8 | 11(11.3)<br>(11.4) ሆኖ የሚቀየር | መዝገቡ በባንኩ መደበኛ የስራ ሰዓት በማንኛውም ባለአክስዮን እና መዝገቡን ለመመርመር ስልጣን በተሰጠው አካል ሊታይ በሚችልበት ሁኔታ በባንኩ ዋና ፅ/ቤት ወይም አብይ ስራው በሚከናወንበት ቦታ ክፍት ሆኖ መቀመጥ አለበት። | • መዝገቡን በባንኩ መደበኛ የስራ ሰዓት ማንኛውም ባለአክስዮን እና መዝገቡን ለመመርመር ስልጣን የተሰጠው አካል ማየት የሚችል ሲሆን ይህም ባንኩ የኤሌክትሮኒክስ መዝገቡን እንዲያሳዩ ፈቃድ በሰጣቸው ባለሙያዎች አማካኝነት በባንኩ ዋና ፅ/ቤት ወይም አብይ ስራ በሚከናወንበት ቦታ ብቻ ይሆናል። |
| 9 | 12(12.1)<br>12.2 ሆኖ የሚቀየር | የአክስዮን መተላለፍ ወይም መዳረግ በአክስዮን መዝገብ መያዝ ይኖርበታል። | • የአክስዮን መተላለፍ ወይም መዳረግ በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት መመዝገብ አለበት። |

ሕብረት ባንክ አ.ማ
የዲሬክተሮች ቦርድ

# የመመስረቻ ጽሁፍ ማሻሻያ የውሳኔ ሃሳቦች

ኅዳር 2018 ዓ.ም

| | | | |
|---|---|---|---|
| 10 | 12(12.2)<br><br>12.3 ሆኖ የሚቀየር | ማንኛውም የአክስዮን መተላለፍ በፅሁፍ ሆኖ ባንኩ በሚያፀድቀው ቅፅ መሰረት መዘጋጀት ይኖርበታል። | • ማንኛውም የአክስዮን የባለቤትነት ዝውውር የሚደረገው በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ውስጥ በሚደረግ የኤሌክትሮኒክስ የምዝገባ ደብተር አማካኝነት ይሆናል። |
| 11 | 12 (12.4)<br><br>12.5 ሆኖ የሚቀየር | አዲስ ባለአክስዮን ሊተላለፍለት ወይም ሊገዛ የሚችለው አነስተኛው የአክሲዮን ብዛት 100 ነው። ይህ የቁጥር ገደብ በፍርድ ቤት ትእዛዝ፣ በውርስ፣ በስጦታ፣ ለባንኩ ሰራተኞች ወይም ለነባር ባለአክስዮኖች የሚደረግ ዝውውርን አያካትትም። | • በመያዣነት፤በዋስትና ተይዞ ወይም ስልጣን ባለው አካል ህጋዊ ገደብ የተጣለበት ካልሆነ በስተቀር በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ያዡ ወይም በተፈቀደው የተውሶ ስም ተይዞ ግዑዝ አልባ የተደረገ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ምንም ክልከላ ሊኖርበት አይገባም። |
| 12 | 17 | አዲስ የተመዘገቡ አክስዮኖች ባለቤቶች በባንኩ የባለአክስዮኖች መዝገብ ጉባኤው ከሚካሄድበት ዕለት ከሶስት ቀናት አስቀድመው የተመዘገቡ መሆን አለባቸው። | • አዲስ የተመዘገቡ የአክስዮን ባለቤቶች በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት የኤሌክትሮኒክስ የምዝገባ ደብተር ጉባኤው ከሚካሄድበት ዕለት ከሶስት ቀናት አስቀድመው የተመዘገቡ መሆን አለባቸው። |
| 13 | 18 | አንድ ባለአክስዮን ለጠቅላላ ጉባኤ አንድ ወኪል በፅሁፍ መወከል ይችላል። ወኪል ለመሆን ባለአክስዮን መሆን አስፈላጊ አይደለም። | • አንድ ባለአክስዮን ለጠቅላላ ጉባኤ አንድ ወኪል በፅሁፍ መወከል ይችላል። በአካል ወይም በውክልና በማንኛውም ስብሰባ ላይ የሚሳተፍ ሰው የራሱን ድምፅ ጨምሮ በአጠቃላይ ከተፈረመው የባንኩ ካፒታል ከአስር በመቶ (10%) በላይ መብለጥ የለበትም። ወኪል ለመሆን ባለአክስዮን መሆን አስፈላጊ አይደለም። |

## 2. **አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት በአዲስ መልክ የሚጨመሩ አንቀጾች**

**አንቀጽ 4 - የሥራ መስክ እና ዓላማ ላይ የሚጨመሩ**

4.7 በአክስዮን ገበያ ውስጥ መሳተፍ፣ ማለትም

4.7.1 በባንክና የካፒታል ገበያ ሕጎችና መመሪያዎች ወሰን ውስጥ እና በተገቢው የተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ፍቃድ እና መስፈርቶች መሰረት፣ የተለያዩ ዓይነት ሰነድ ሙዓለንዋዮችን ማውጣት፣ የእዳ ሰነድ ሙዓለ ንዋይ ማውጣት (ለሽያጭ ማቅረብ) እና መገበያየት፣

4.7.2 እንደ አግባብነቱ በሕግ በተመለከተው መሰረት ቀጥሎ በተመለከቱትና ሌሎች በሕግ በተፈቀዱት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት ሥራ ላይ መሰማራት፡-

4.7.2.1 የኢንቨስትመንት ባንክ አገልግሎት መስጠት፣

4.7.2.3 የሠነደ ሙዓለንዋዮች ገበያ ጠባቂ (securities custodian) አገልግሎት መስጠት፣

4.7.2.4 የሠነደ ሙዓለንዋዮች ገበያ ከፋች (market making) አገልግሎት መስጠት፣

4.7.2.5 የሠነድ ሙዓለንዋዮች ፖርትፎሊዮ አስተዳደር እና በሕግ የተፈቀዱ ሌሎች የካፒታል ገበያ አገልግሎት መስጠት፤

**አንቀጽ 7 ሆኖ የሚጨመር**

**አንቀጽ 7- አክሲዮኖች የሚወጡበት ዋጋ፣ የአክሲዮኖቹ አከፋፈልና ቀሪ ዋጋቸዉ ላልተከፈሉ አክሲዮኖች ስለሚኖር ኃላፊነት**

7.1 አክሲዮን ማህበሩ አክሲዮኖችን ከተፃፈባቸዉ ዋጋ ባነሰ ዋጋ ማዉጣት አይችልም ።

7.2 አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባዔው የሚፈቅደው የካፒታል ጭማሪ መሠረት በማድረግ እና አግባብነት ያለውን ህግና መመሪያ ተከትሎ አክሲዮኖች ከተጻፈባቸዉ በሚበልጥ ዋጋ እንዲወጡና አክሲዮኖች ለሽያጭ የሚወጡበትን ዋጋ የዳይሬክተሮች ቦርድ ይወስናል።

7.3 የአዲስ አክሲዮኖች ግዢ ሲፈፀም ፣ የአክሲዮን ገዢው የፈረማቸዉን አክሲዮኖች ዋጋ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት መከፈል ይኖርበታል።

7.4 የተፈረመ የአክሲዮን ባለይዞታ ፣ ከዚህ በፊት የነበረ ባለአክሲዮን እና የአላባ ጥቅም መብት ያለው ማንኛዉም ሰው ፣ በንግድ ሕጉ እና በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን መመሪያዎች መሠረት ፣ ተፈርመው ላልተከፈለ አክሲዮኖች ክፍያ ለባንኩ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ይሆናሉ ።

7.5 ዋጋቸዉ ያልተከፈለ አክሲዮኖች ቀሪ ክፍያ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ይህንኑ በተወሰነዉ ቀን ካልተከፈለ የንገድ ሕግ አንቀጽ 289 ከንዑስ አንቀጽ 3 እስከ 7 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

ሕብረት ባንክ
Hibret Bank
በሕብረት እንደግ!

hibretbank.com.et

# የመመስረቻ ጽሁፍ ማሻሻያ የውሳኔ ሃሳቦች

## ኅዳር 2018 ዓ.ም

**አንቀጽ 11 የባለአክስዮኖች መዝገብ ላይ የሚጨመር**

11.1. ሁሉም የባንኩ አክስዮኖች ግዑዝ አልባ መደረግ እና በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት መመዝገብ አለባቸው።

**አንቀጽ 12 የአክስዮን መተላለፍ ላይ የሚገባ**

12.1 ማንኛውም ባለአክሲዮን ግብይት የሚያካሂደው በተፈቀደለት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭ/አከናዋኝ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ወይም ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ በኩል ብቻ ይሆናል።

12.6 የዲሬክተሮች ቦርድ ባንኩ አዲስ አክስዮን በሚያወጣበት ጊዜ አንድ ባለአክስዮን ሊገዛ የሚችለውን አነስተኛ የአክስዮን መጠን ሊወስን ይችላል።

**አንቀጽ 24.2 የዲሬክተሮች ቦርድ ስልጣንና ተግባር ላይ የሚጨመሩ**

24.2.9 ባንኩ በሕግ በተፈቀደ በማንኛውም አይነት የካፒታል ገበያ በአገልግሎት ሰጪነት፣ በካፒታል ገበያ እንቅስቃሴ ላይም ሆነ ሌሎች በሕግ በተፈቀዱ ስራዎች ላይ ተሳትፎ በማድረግ አገልግሎት መስጠት እንዲችል፣ ተቀጥላ አባላቶች እንዲቋቋሙ ወይም በሥራ ላይ ባለ ወይም አዲስ በሚቋቋሙ ኩባንያዎች ውስጥ የአክሲዮን ድርሻ እንዲገዛ መፍቀድ፣

24.2.10 ባንኩ አክስዮኖችን በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን ምዝገባ ለማከናወን እንዲችል፣ ከዚሁ ጋር የተያያዙ ማናቸውንም ጉዳዮችና ተግባራትን ማከናወን፣ውሳኔ መስጠት፣ ማረጋገጫዎች መስጠት፣ አክሲዮን ለሽያጭ የሚቀረብበትን ዋጋ መወሰን፣ የአክስዮኖች ሽያጭ ማቅረቢያ ጊዜን መወሰን ፣ በሚመለከታቸው አካላት የማስመዝገብ፣ ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ግብይትም ሆነ በተፈቀደለት የሰነደሙዓለ ንዋይ ገበያ እንዲመዘገብ መወሰንና ከዚህ ጋር የሚያያዙ ክንውኖች ላይ ውሳኔ መስጠት፣

24.2.11 በተገቢ ተቆጣጣሪ ተቋማት በሕግ በተቀመጠው መሠረት በቋሚነት መረጃን ይፋ የማድረግ ግዴታዎች መከናወናቸውን፣እንዲሁም ሌሎች የኮርፖሬት አስተዳደር ግዴታዎችን ጨምሮ ሁሉም የካፒታል ገበያ ሕጎች በተሟላ ሁኔታ መከናወናቸውን ማረጋገጥ፣

24.2.12 በካፒታል ገበያ እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሳተፍ የሚያስፈልጉ ወይም ተያያዥ የሆኑ ሁሉንም በሕግ የተፈቀዱ እርምጃዎችን በመውሰድ ውሳኔ መስጠት፤

**ማስታወሻ፡-**

- የመመስረቻ ጽሁፉ የተሻሻለው በሚከተሉት አዲስ በወጡ እና በተሻሻሉ ሕጎች መሠረት ነው፤
  1. የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 1360/2017 አንቀጽ 12/2፣አንቀጽ 13/ሀ እና ለ
  2. የካፒታል ማርኬት ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013
  3. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የኮርፖሬት ገቨርናንስ መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024
  4. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ የባንኮችን ኢንቨስትመንት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር SBB/92/2024/4.2.2
  5. በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን የወጡ መመሪያዎች፡-
     - 5.1. ለህዝብ የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዑዝ አልባ የማድረግ (Dematerialization) መመሪያ ቁጥር 1047/2017 ክፍል 1 ቁጥር 2 /4፣ ክፍል 2 ቁጥር 5/3፣ክፍል 3 ቁጥር 11/2፣ክፍል 4 ቁጥር 2፣ክፍል 5 ቁጥር 16/1
     - 5.2. ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለሕዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ቁጥር 1030/2017
     - 5.3. የካፒታል ገበያ ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ 980/2016

- የመመስረቻ ጽሁፉ የአንቀጽ ቁጥሮች በማሻሻያው መሠረት በመሸጋሸግ የሚስተካከሉ ይሆናል።

**ሕብረት ባንክ አ.ማ**
**የዲሬክተሮች ቦርድ**